# ክራር፡ይክረር



ክራር፡ይክረር፤ማሲንቆዉም፡ድምጹ፡ይጉረር፣
ፅናፅኑም፡አያንቃጭል፡ደፈር፡ይበል፡ጀግን፡ጠንክር፣
ከበሮዉም ፡እምቢ፡ይበል፡ይፈናጠር፡ከሮ፡ይንዘር፣
ከዜመኛው፡ተነጥሎ፡የምን፡ቃና፡የምን፡ማዝመር፡፡

ጥኡም፡ዜማ፡በተምሳሌ፡ከታሪክ፡ጋር፣
ፍቅርን፡ሰብከኸ፡የመገብከን፡ልክ፡እንደማር፣
ጥርስ፡ገብተህ፡በአባ፡ጳውሎስ፡አላሙዲን፣
በወያኔ፡ህገ፡አራዊት፡መንጋ፡ቡድን፣
በአንድ፡ጀንበር፡ቲያትር፡ሠርተው፡፡ተተውኖ፣
ጭዳ፡ጥለው፡አስፋልት፡ላይ፡ተከውኖ፣
ለአንተ፡ፍዳ፡ቢያወርሱህም፣
አገር፡ህዝብህ፡አይረሳኸም፣
ምልጃ፡ይዘዋል፡ምዕመናኑም ፣
ቤተ፡መስጊድ፡ገዳማቱም ፡፡

ባህር፡ማዶ፡ፈረንጅ፡አገር፡ያለህ፡ወገን ፣
መላ፡ምታ፡ለዚህ፡ሙሴ፡ከጎኑ፡ሁን፣
አትጨፍር፡ዳንሱ፡ይቁም፡ቴዲ፡ታስሮ፣
ክራር፡ይክረር፣ማሲንቆዉም፡ድምጹ፡ከሮ፣
ድምትምታዉን፡ያጎልብተው፡ያ ከበሮ፡፡፡

ድረ፡ገጾች፡የምን፡ክፍተት፡አስተባብሩ፣
ፓልቶክ፡ክፍሎች፡ጀግን፡በሉ፡ተጠራሩ፣
ወሬ፡ይቁም፡ለድል፡ፍሬ፡ታሪክ፡ሥሩ፡፡

እንግዳ፡ታደሰ_ኖርዌ